## Art & Culture: ሦስተኛው ሺሕ በ2001 ይገባል፤ የበዓል ዝግጅቱ በ2000 ይደረጋል





አቶ ሥዩም በረደድ

የኢትዮጵያ አዲሱ ሺሕ ዓመት /ሚሊኒየም/ የሚገባው በ2001 መስከረም መሆኑና የዋዜማ ክብረ በዓል ከጳጉሜን 6 ቀን 1999 እስከ ጳጉሜን 5 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች እንደሚከበበር ብሔራዊ ጽሕፈት ቤቱ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ሚሊኒየም አከባበር ብሔራዊ ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሥዩም በረደድ ለሪፖርተር ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ 2001 ዓ.ም የአዲስ አንድ ዓመት፣ አሰርት ዓመት፣ ምእት ዓመትና የሺሕ ዓመት ተጣምረው የሚነሱበት የዘመን መሸጋገሪያ በመሆኑ በተለየ መልኩ እንደሚከበር አስረድተዋል።

በአምሳ ትውልድ አንድ ጊዜ የሚመጣው የሺሕ ዓመት ክብር በኢትዮጵያ ሦስተኛው ሺሕ /ሚሊኒየም/ መግቢያ ላይ በመገኘቱ የትውልድ ዘመን ዱላ ቅብብሉ የመጨረሻውን ገመድ በጥሶ የሚገባ ጫፍ ላይ ያለ ትውልድ ስለሆነ በልዩ አተኩሮ ለማክበር በዝግጅት ላይ መሆኑ አቶ ሥዩም ገልጸዋል።

ለአንድ ዓመት መቀበያ አንድ ቀን ዋዜማ እንዳለው ሁሉ ለአንድ ሺሕ ዓመት አንድ ዓመት ዋዜማ ማድረጉ አስፈላጊነቱን የጠቆሙት አቶ ሥዩም በዓሉ፣ በዓል ማክበርን በአንድ ጎኑ ሁለተኛ ደግሞ ቅርስን ለትውልድ መተው ላይ ያተኮረ መሆኑ አመልክተዋል። ቅርሱ ላይ ሕዝቡን ያሳተፉ እንቅስቃሴዎች እንደሚኖሩ አንገብጋቢ የሆኑ የአካባቢ ጥበቃና የደን ሁኔታዎች ስላሉ አገር በቀል ዛፎችን እንደ ሐውልት የሚተከሉበት አጋጣሚ የሚፈጠርበት እቅድ መውጣቱንም አስረድተዋል።

በየክልሉ ዋና ከተሞች የሚሊኒየም ፖርኮች ለመስራት የመሰረት ድንጋይ በችግኞች ተጥሏል እያንዳንዱ ፖርክ ሁለት ሺሕ ዛፎች በተለይ ይጠፋሉ ተብለው የሚታሰቡት ሀገር በቀል ዛፎች እንዲኖሩት ታቅዷል።

በየፖርኩ የየብሔረሰቡን ቅርሶች የሚያስቀምጡበት ማዕከልም ይኖራል። መናፈሻ ውስጥ የሚገባው የሚያይበትና ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት ሥራው ተጀምሯል።

በዋዜማው በትልቅ ድምቀት በክልል ዋና ከተሞች በተዋረድ ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ የሚከበሩ የበዓል ዝግጅቶች ይኖራሉ። የየብሔረሰቡን ባህል ቅርስ ሙዚቃ የሚያሳዩ ዝግጅቶች ከመኖራቸውም በላይ ከተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የሚመጡ ተሳታፊዎችም ይገኛሉ። የክብረ በዓሉ አንዱ ተግባር የአገሪቱን ገጽታ ማደስ ስለሆነ ዓለም፡- ኢትዮጵያ ሦስቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች ክርስትና አይሁድና እስልምና ከሺሕ ዓመታት በላይ ተከባብረው የኖሩበት አገር መሆኗን እንዲረዳው ሕዳሴ /ሬኔሳንስ/ እንዲፈጥር ነው።

ክብረበዓሉ ለመጪው ትውልድ ቅርስ የመተው አጋጣሚ እንደሚጥር ያወሱት ዳይሬክተሩ አንዱ ቅርስ በሚሊኒየም ስም የሚጠራ ልዩ ትምህርት ቤት ማዘጋጀት ነው ብለዋል። ሚሊኒየም ትምህርት ቤቱ «የላቀ ችሎታ ያላቸው ሆነው በአቅም ማነስ ትምህርታቸውን ለመከታተል ለማይችሉት በአዳሪ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩበት ሁኔታ ይፈጥራል» እንደ አቶ ሥዩም አገላለጽ። የሚሊኒየሙ ክብረ በዓል የእግር ጉዞ፣ ታሪካዊ ሥፍራዎች ጉብኝት፣ የኢትዮጵያን ታላቅ ሩጫ ያካተተ ነው። በተለይ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ቦታ ስለሆነች፣ ሉሲ /ድንቅነሽ/ የተገኘችበት ሥፍራ ሀዳር፣ በቅርቡ «ሰላም» የተገኘችበት ቦታ ዲኪካ የጉብኝቱ አንድ አካል መሆኑንም አክለው ገልጸዋል።

የሉሲ ወደ አሜሪካ መጓዝ በዓሉን አያደበዝዘውም ወይ? ለሚለው ጥያቄ ዳይሬክተሩ በሰጡት ምላሽ «እንደ ጽሕፈት ቤቱ እምነት ሉሲ ለሚሊኒየሙ እዚህ ቆይታ ብናከብር ደስተኛ ነን። ጥያቄውን ለሚመለከተው ክፍል እናቀርባለን፤ በቅርቡ አዲስ የተገኘውና ከሉሲ በዕድሜ የምትበልጠዋ «ሰላም»ን በበዓሉ ለማስተዋወቅ ጥሩ አጋጣሚ ነው። የሚሊኒየሙም ገጸ በረከት ነች» ብለዋል።

በሚሊኒየሙ በዓል ወቅት ከደራስያንና ከሥነ ጥበባት ብሔራዊ ማኅበራት ጋር በሚኖረው ግንኙነት በቅርስ በታሪክ ዙሪያ ውይይቶች የሚካሄዱባቸው ኮንፈረንሶች እንደሚካሄዱ ለወጣቱ ትውልድ አርአያ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡትን ታላላቅ ሰዎች የማስተዋወቅና የማወደስ ተግባር እንደሚኖር ያወሱት ዳይሬክተር ብዙነኑ አርሶ አደር /ገበሬ/ ባህሉን የሚያሳይበት፣ ምርቱን የሚያስተዋውቅበት፣ ኤግዚቢሽኖችና ስብሰባዎች መታቀዱን ገልጸዋል።

በቅርስነት ለማስተላለፍ ከታሰቡት መካከል የቡና ምንጭ በሆነችው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የቡና ዝርያዎችና የቡና ባህልን የሚያሳይ ሙዚየም ኢትዮጵያን በአትሌቲክስ ስመጥር ያደረጓት ጀግኖች አትሌቶች የሚዘከሩበት የስፖርት ሙዚየም ይገኙበታል።

ምክር ቤቱ ከመንግስት ከተፈቀደለት በጀት ሌላ ለነደፈው እቅድ ማስፈፀሚያ ከተለያዩ የአገር ውስጥ ስፖንሰር አድራጊዎች የሚያገኝ መሆኑን አቶ ሥዩም ጠቁመዋል።

የተለያዩ ተቋማት ሚሊኒየሙን ለማክበር በብሔራዊ ጽ/ቤቱ ሥር ካለ የፕሮጀክት ክፍል ግንኙነት በማድረግ በቅንጅት ለመሥራት ፕሮጀክቶቻቸው እንደሚያስገመግሙም ዳይሬክተሩ ሳይገልጹ አላለፉም።

«ሚሊኒየም» የሚለው ስያሜ ሺሕን ዓመት ለመግለጽ ላቲኑ የሚጠቀምበት ቃል መሆኑን ተመሳሳይ ቃል በመፈለግ አጠ ራሩን ለመተካት በተለያየ ቦታ እየተሞከረ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሥዩም፣ ቃሉ ሕዝቡ ውስጥ ስለገባና ስለተለመደ እንደሌሎቹ የውሰት ቃላት፣ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሚሊኒየምንን ተቀብለናል ጽ/ቤታችንም ሕጋዊ መጠሪያ እርሱን ያመለክታል ብለዋል።

የሚሊኒየሙን መምጣት አስመልክቶ በሸራተን አዲስ መግቢያ ላይ የተሰቀለው «የዚህ ያህል ቀን ቀረው» ሰሌዳ ላይ ዳይሬክተሩ በሰጡት አስተያየት «ሆቴሉ በሰሌዳው የሚሊኒየም ክብረበዓል መጣ በሚለው መንፈስ ለማሳየት ከሆነ ዓመቱን ሙሉ ስለሚከበር ችግር የለበትም። አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም የሚገባው ግን በ2001 ነው» ብለዋል። ጽ/ቤቱ 2000 ዓመትን እንደልዩ ዓመት የመሸጋገሪያ ምዕራፍ ለመጠቀም እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም አክለው ገልጸዋል።

የሚሊኒየሙን በዓል በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያን በተደራጀ መልኩ በኅብረት ለማክበር እንዲችሉ መገናኛ ብዙኀን ተገቢ ቅስቀሳ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው የጠቆሙት አቶ ሥዩም፣ በዓሉ ጥሩ የተባሉ ባህሎችን በማጉላት፣ ለታሪክ መልካም ነገር ማትረፍ እንደሚገባው አሳስበዋል።

በሔኖክ ያሬድ

Posted on Sunday, November 19 @ 14:02:36 EAT by staff